የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፳
አዲስ አበባ የካቲት ፲፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No. 20
ADDIS ABABA, 22nd February ,2017

<u>ማውጫ</u>

**CONTENT**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ/፪ሺ፱ ዓ.ም

ለገናሌ ዳዋ ፫-ይርጋለም ፪ - ወላይታ ሶዶ ፪-ሐዋሳ ፪ የኃይል ማስተላለፊያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከቻይና የኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ……………………………………ገጽ ፱ሺ፭፻፵፩

Proclamation No. 1000/2017

Export –Import Bank of China Loan Agreement Genale Dawa III-Yirgalem II- Wolayita Sodo II-Hawassa II Power Transmission Project Ratification Proclamation ……………………………………………….Page 9541

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ/፪ሺ፱

**<u>በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና የኤክስፖርት - ኢምፖርት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>**

ለገናሌ ዳዋ ፫-ይርጋለም ፪ - ወላይታ ሶዶ ፪ ሐዋሳ ፪ የኃይል ማስተላለፊያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፪፻፵፱ ሚሊዮን ፫፻፳፫ ሺ ፸፭ ከ፴፬ የአሜሪካን ዶላር (ሁለት መቶ አርባ ዘጠኝ ሚሊዮን ሦስት መቶ ሃያ ሦስት ሺ ሰባ አምስት ከሠላሳ አራት የአሜሪካን ዶላር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና የኤክስፖርት - ኢምፖርት ባንክ መካከል ጥር ፲፯ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም በቤጂንግ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፴ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ

PROCLAMATION No. 1000/2017

**<u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE EXPORT-IMPORT BANK OF CHINA</u>**

**WHEREAS**, a loan agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export-Import Bank of China stipulating that the Export-Import Bank of China Provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan in an amount not exceeding USD 249,323075.34 (two hundred forty nine million three hundred twenty three thousand seventy five and thirty four United State Dollars) for financing the Genale Dawa III-Yirgalem II-Wolayita Sodo II- Hawassa II power Transmission Project was singed in Beijing on the 27th of December 2016;

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 7th day of February 2017;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡-

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ " ለገናሌ ዳዋ ፫-ይርጋለም ፪ -ወላይታ ሶዶ ፪-ሐዋሳ ፪ የኃይል ማስተላለፊያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከቻይና የኤክስፖርት - ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና የኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል ጥር ፲፯ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም በቤጂንግ የተፈረመው ቁጥር PBC No. (2016) 31 Total No.(419) 1420303052016212669 የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፪፻፵፱ ሚሊዮን ፫፻፳፫ ሺ ፸፭ ከ፴፬ የአሜሪካን ዶላር (ሁለት መቶ አርባ ዘጠኝ ሚሊዮን ሦስት መቶ ሃያ ሦስት ሺ ሰባ አምስት ከሠላሳ አራት የአሜሪካን ዶላር)በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ የካቲት ፲፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. Short Title**

This Proclamation may be Cited as the "Export-Import Bank of China Loan Agreement Genale Dawa III-Yirgalem II- Wolayita Sodo II-Hawassa II Power Transmission Project Ratification Proclamation No. 1000/2017."

**2. Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement No. PBC No. (2016) 31 Total No. (419) 1420303052016212669 singed on the 27th day of December 2016 the Government of the Federal Democratic Repubulic of Ethiopia and the Export- Import Bank of China is hereby ratified.

**3. Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation**

Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of USA 249,323,075.34 (two hundred forty nine million three hundred twenty three thousand seventy five and thirty four United State Dollars in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 22nd day of February , 2017.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**